## የሰፕቴምበር 2014 QuickNotes ዜና መልእክት 3ኛ መድብል

### MCPS የተሻለ ድር ጣብያ ጀመረ፣ አዲስ የሞባይል መተግበሪያ (App)

MCPS ለወላጆች፣ ሰራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ እና ለማህበረሰብ አባላት የሚያስፈልጋቸውን የት/ቤት መረጃ በቀላሉ ማግኘት ለማስቻል የተተለሙ ሁለት አይነተኛ መነሳሺያዎች ጀምሯል።

MCPS የዲስትሪክቱን ድር ጣብያ እንደገና ቀይሶታል፣ ከጊዜው ጋር የሚሄድ መልክ ብቻ አይደለም ያለው፣ መረጃን ለማግኘት ይበልጥ ተደራጅቷል እንጂ። MCPS በአንድ ንኪት ወደ መረጃና ዜና የሚያደርስ ነፃ የሞባይል መተግበሪያ በተጨማሪ ጀምሯል። መተግበርያው በአይፎንእና በአንድሮይድ የተመሰረቱ ቴሌፎኖች ሊደረስበት ይቻላል፣ ለአማዞን የመተግበርያ ሱቅም (Amazon app store) ማግኘት ይቻላል።

ማሻሺያዎች የተደረጉት በተጠቃሚዎች አስተያየት፤ በአሁኑ ወቅት አሉ የተባሉ የድርጣብያ ንድፍና አደረጃጀት ልምዶች፤ ሰዎች የMCPSን ድርጣብያ እንዴት እንደሚደርሱበትና እንደሚጠቀሙበት የመረጃዎች ጥንቅር በመመስረት ነው። በትምህርት አመት ውስጥ፣ የMCPS ድርጣብያ በአማካይ 1.7 ሚልዮን የገፅ እይታዎች በሳምንት ውስጥ ያገኛል ከሞባይል መሳርያዎች የሚደርሱበት ሰዎች ቁጥርም እያደገ ነው። ከ 2012 ጀምሮ፣ የሞባይሎች ጉብኝት ወደ MCPS ድር ገፆች በ400 በመቶ በላይ አድጓል።

በኤፕረል 2013፣ MCPS የድርጣብያ ግንባታውን ምላሽ-ሰጭ (responsive) የድር ንድፍ በመጠቀም ጀመረው፣ ይህም ድርጣብያውን ለመገልገል ጥቅም ላይ በሚውለው መሳርያ መሰረት ራሱን የሚያስተካክል ነው። ይህም ማለት አንድ ተጠቃሚ ከጣብያው ጋር በኮምፒውተር የሚያደርገው የግንኙነት መንገድ ከታብሌት ወይም ከስማርትፎን የተለየ ነው፣ ነገር ግን ይዘታው ያው ነው።

የተሻሻለው ድርጣብያ ይበልጥ ተንቀሳቃሽና ዘመናዊ ቀለሞች አሉት፣ ከበለጠ ስልታዊ የስእሎችና የምስሎች አጠቃቀም ጋር። ጣብያው በተጨማሪ በገፁ ላይኛው ክፍል በርካታ ይዘቶች አስፍሯል እናም በአሁኑ የላቀው የድር አነዳደፍ ልምድ የሆነ "የረድፍ-በረድፍ (tiled)" መልክ አለው። እነዚህ የሞድ ንጥረነገሮች (style elements) በመቶዎች በሚቆጠሩ ነባር ድር ገፆች ላይ ተግባራዊ ሆነዋል፣ እናም በመጪ ገፆች ላይም ጥቅም ላይ ይውላሉ።

[በተጨማሪ ይማሩ]

[በአዲሱ ድርጣብያ አጭር ቪድዮ ይመልከቱ]

## የእግረኛን ደህንነት በት/ቤት ማራመድ

ተማሪዎችን ያሚያካትት የእግረኛ ግጭቶች ለመቀነስ በካውንቲ አቀፍ ደረጃ በሚከናወን አዲስ የትምህርት ፕሮግራም MCPS ከMontgomery County የትራንስፖርት መምርያ ጋር በመሻረክ ላይ ይገኛል።

የትምህርቱ ፕሮግራም፣ You Only Live Once (አንድ ጊዜ ብቻ ነው የምትኖረው) (YOLO)፣ ስለ ሰላማዊ የእግረኛ ልምዶችና ትኩረት ሳይሰጡ መራመድ አስጊነት ንቃት ለመስጠት በ Montgomery County የትራንስፖርት መምርያ የዳበረ ነው። የYOLO ዘምቻ አካል በመሆን እያንዳንዱ የMCPS ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት የት/ቤቱን ማህበረሰብ በሰላማዊ የአግረኛ ልምዶች ለማበረታት የሚያግዙ የተለያዩ መገልገያዎች የያዘ የመሳርያዎች ጥቅል ይሰጠዋል።

የMCPS ወላጆች ከልጃቸው(ልጆቻቸው) ስለ ትኩረት ማጣት አደጋዎች እና መንገድ ከማቋረጣቸው በፊት መሳርያዎችን ስለ ማጥፋት አስፈላጊነት በመነጋገር በዚህ ጥረት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

ስለ YOLO ዘመቻ፣ እንዲሁም ስለ አብዛኛዎቹ መገልገያዎች መረጃዎች፣ በ[www.montgomeryschoolsmd.org/safety](www.montgomeryschoolsmd.org/safety) ይገኛሉ

የት/ቤት አውቶቡሶች ተማሪዎችን ሲያሳፍሩና ሲያወርዱ አሽከርካሪዎች መቆማቸውን ለማረጋገጥ ለተማሪዎች ደህንነት የMCPS እና የMontgomery County የፖሊስ መምርያ ተጨማሪ የትኩረት ጥረት ነው። በርካታ የMCPS የት/ቤት አውቶቡሶች አውቶቡሶችን የሚያልፉ መኪናዎችን የሚያነሱ አውቶማቲክ ካሜራዎች አሁን ተገጥመውላቸዋል። ካሜራው አንድ ጥሰት ከለየ፣ እናም በፖሊስ ከተረጋገጠ፣ የ$125 የመቅጫ ቲኬት ለተሽከርካሪው ባለንብረት ይላካል። ካሜራዎቹ የካውንቲውን ማንኛውንም ክፍል በሚያገለግሉ አውቶቡሶች ላይ ተገጥመዋል።  ቃሉን በማሰራጨት ተባበሩ። አብረን፣ በMCPS አውቶቡሶች የሚጓዙ የሁሉንም ልጆች ደህንነት ማረጋገጥ እንችላለን።

[PSAን ተመልከቱ/ታዘቡ]()

## አማራጮች፣ ለወላጆች መስመር ላይ መገልገያ

የ2014-2015 የ*Options* (አማራጮች) መመርያ ተማሪዎችንና ቤተሰቦቻቸውን በMCPS በኤሌሜንታሪ፣ መካከለኛ፣ እና ከፍተኛ ት/ቤት ደረጃዎች ስለሚገኙ የተለያዩ ፕሮግራሞች ለመማር ለማገዝ የተተለመ ነው። ተማሪዎች የትም ቦታ ይኑሩ አብዛኛዎቹን እነዚህን ፕሮግራሞች ሊያገኟቸው ይችላሉ። እያንዳንዱ ፕሮግራም በተማሪ ፍላጎትና ተነሳሽነት የተመሰረቱ የበለፀጉ የመማር እድሎች እንዲሰጥ የተተለመ ነው። የ*Options* መመርያ ስለሚገኙ እድሎች መጣቀሻ

ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣ ነገር ግን በካውንቲ የሚገኘውን እያንዳንዱን/ሁሉንም ልዩ ፕሮግራም አያጠቃልልም። መመርያውን በሙሉ በሚያነቡበት ወቅት ወላጆች የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲያገናዝቡ ይበረታታሉ፡-

- ለልጄ ከሁሉ የበለጠ የመማርያ አካባቢ/ሁኔታ ምንድን ነው?
- እዚህ መመርያ ውስጥ ከተዘረዘሩት ፕሮግራሞች ምንኞቹ ናቸው ከልጄ ፍላጎቶችና ጥቅሞች ጋር መልካም ተመጣጣኝ የሚመስሉት?
- ከቤታችን አካባቢ ካለው ት/ቤት ልጄ ሊያገኛቸው የሚችል አማራጮችን አገናዝቤአለሁ ወይ?

መመርያ መስመር ላይ በ ቻይኒዝ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያን፣ ስፓኒሽ እና ቪዬትናሚዝ ይገኛል።

## በMontgomery County አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን ይሳተፉ

የMontgomery County 28ኛ አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት ለኦክቶበር 18-26 2014 ተወስኗል። የMCPS ተማሪዎች እንዲሳተፉ እና ከPTAአቸው ወይም ከማህበረሰብ በጎ አድራጎት ጋር አብረው በመስራት የአገልግሎት ፕሮጀክት እንዲቀይሱ ይበረታታሉ።

ተማሪዎች በት/ቤታቸው የፅዳት ወይም የአካባቢ አትክልት ፕሮጀችት፣ የአገልግሎት መማርያ በአል፣ ለቤትየለሾች አነስተኛ የእግር ጉዞ ወይም ሌላ ስሜታቸውን የሚነሽጥ የሆነ ፕሮግራም ፕላን ማድረግ ይችላሉ። ይህ ለወላጆችም ሆነ ለተማሪዎች አንድ ላይ ለማገልገል መልካም አጋጣሚ ነው።

ተማሪዎች በMontgomeryserves.org ፕሮጀክታቸውን ማስመዝገብ ወይም ለፈቃደኝነት መመዝገብ ይችላሉ። ተማሪዎች ለዚህ ስራ Student Service Learning (SSL) (የተማሪ አገልግሎት ትምህርት) ሰአቶች ማግኘት ይችላሉ።

## የNAACP የወላጆች ምክርቤት መነሻ (Kickoff) ስብሰባ ሊያካሂዱ ነው

የNAACP የወላጆች ምክርቤት መነሻ (Kickoff) ስብሰባ ከ5–8:30 p.m. ሰኞ፣ ኦክቶበር 6 በRichard Montgomery High School ይካሄዳል። ይህ ክውነት ወላጆችን፣ የMCPS መምህራንን እና ርእሰመምህራንን የወላጅ ተሳትፎን ለመኮትኮትና የተማሪን ግኝት ለማራመድ ሀሳብ እንዲጋሩ ያሰባስባቸዋል።

ተሳታፊዎች ከአራት ትምህርታዊ ስብሰባ ርእሶች ህዝባዊ ደህንነት/የተማሪ ዲሲፕሊን፣ የአካዴሚያዊና ማህበራዊ ትምህርት አፈፃፀም ተግዳሮት፣ ወላጅ እና መህበራዊ ተሳትፎ፣ እና ቴክኖሎጂ መካከል መምረጥ ይችላሉ። የማህበረሰብ አገልግሎቶችና መገልገያዎች ለማጉላት በክውነቱ ወቅት የማህበረሰብ መገልገያ በአል በተጫማሪ ይካሄዳል። ምዝገባ መስመር ላይ ይኖራል። የመመዝገቢያ ገደብ ሀሙስ፣ ኦክቶበር 2 ነው።

**የተማሪ አመራርና የአገልግሎት እድሎች ይገኛሉ**

የMaryland Student Page (የሜሪላንድ ተማሪ ገፅ) ፕሮግራም በአናፖሊስ ለሚካሄደው የ2015 የሜሪላንድ ጠቅላላ ስብሰባ (Maryland General Assembly) የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት የመጨረሻ ክፍል ተማሪዎች እየፈለገ ነው። ቢያንስ 16 አመት የሞላቸው የሜሪላንድ የከፍተኛ ዓመት ተማሪዎች ለማመልከት ብቁ ናቸው። እንግዳ ተቀባዮች በሴኔት ወይም በሃውስ ኦፍ ደለጌትስ ለ13 ሳምንቶች ይመደባሉ ለያንዳንዱ ያገለገሉበት ቀን $55 የኪስ ገንዘብ ይሰጣቸዋል። የማመልከቻ ማስገቢያ የጊዜ ገደብ አርብ፣ ኦክቶበር 24 4 p.m. ነው። ማመልከቻዎች በ[MCPS Office of Student Affairs (የተማሪ ጉዳይ ፅ/ቤት) ድርጣብያ] ሊገኙ ይችላሉ።

ያለቁ ማመልከቻዎች ወደ Katie Rossini (ካቲ ሮሲኒ)፣ 12900 Middlebrook Road, 3rd Floor West, Germantown, MD 20874 መላክ አለባቸው።

**ተማሪ-ያደሰው የኮምፒውተር ላቦራቷር (Student-Refurbished Computer Lab) ለበጎ አድራጎት ሊሰጥ ነው**

Montgomery County Students Information Technology Foundation, Inc. (የተማሪዎች መረጃ ቴክኖሎጂ ተቋም ኩባንያ) (ITF) የታደሰ ኮምፒውተር Montgomery County ለሚገኝ ለአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይሸልማል። ላቦራቷሩ ስርዓተ ክወናዎች (operating systems) ያላቸው ስድስት የታደሱ ኮምፒውተሮች፣ ዝርግ LCD ማሳያዎች (monitors)፣ የቁልፍ ሰሌዳዎች (keyboards)፣ መዳፊቶች (mice)፣ እና አንድ ማተሚያ ይይዛል።

የበጎአድራጎት ድርጅቶች ማመልከቺያዎች አርብ፣ ኦክቶበር 3 ገቢ መሆን አለባቸው የሚገኙትም በITF ድርጣብያ፣ ፌስቡክ ገፅ (foundationsfb.org) ወይም ከKelly Johnson (ኬሊ ጆንሰን) በ301-929-2197 ነው።

የተሞሉ ማመልከቻዎች ወደ ITF፣ በተለይ ለKelly Johnson በፖስታ አድራሻ 12501 Dalewood Dr., Room 1116, Silver Spring, MD, 20906፣ ወይም በኢሜይል ወይም በፋክስ ቁ. 301-929-2192 ገቢ መደረግ አለባቸው የስጦታው ስነስርአት ሀሙስ፣ ኖቬምበር 20 በClarksburg High School ይከናወናል።

ITF በMontgomery County ቢዝነስና የባለሙያ ማህበረሰብ እና በMCPS የተመሰረተ ትርፍ-የለሽ (የበጎ አድራጎት) ድርጅት ነው። ፕሮጀክቱ ለITF ተማሪዎች የኮምፒውተር ስርአቶች ለማንቀሳቀስና ለመጠገን የልምምድ እድል ይሰጣል።

MCPS በዜናዎች

ጥቂት ትርፍ ደቂቃዎች አለዎትን? እንግዲያስ ስለMCPS ወቅታዊ ርእሰ አንቀጾች፣ ቪድዮዎች እና የጋዜጣ መግለጫዎችን ይከታተሉ።

*ቪድዮዎች*

Dyan Harrison (ዳያን ሀሪሰን) የአመቱ ረዳት ርእሰመምህር ተብሎ ተሰየመ
የEinstein HS መምህር የካውንቲው "የአምቱ መምህር" ተብሎ ተሰየመ
ተማሪዎች የConstitution Day (ህገመንግስት ቀን) አከበሩ
እለቱን በትክክለኛነት መጀመር
የእግረኛ ደህንነት ት/ቤት ማራመድ

*MCPS በዜናዎች*

የሞንጎመሪ ት/ቤቶች የተማሪ እንቅፋቶች ምልክቶች ለመያዝ በአዲስ መሳርያ መጠቀም
ከBlair High ሁለት ግለሰቦች የፊዚክስ የብር ሜዳልያ አሸነፉ
Broad Acres Elementary በቀድሞ ርእሰመምህር ክብር እንደገና ተሰየመ
ህፅኑን ፖሊስ ተገናኙ
የTakoma Park ት/ቤት አንድ ሚልዮን ዶላር ያሸነፈ መምህር ደስታ ይካፈላል

የSCUP ስብሰባ ተሳታፊዎች ብዛት መዝገብ ሰበረ
በሜሪላንድ ቁርስ የሚበሉ ተማሪዎች ቁጥር ለመጨመር ተጨማሪ ጥረት
60 የላቲኖ ተማሪዎች የኮሌጅ ስኮላርሺፕ ተቀበሉ

*የጋዜጣ መግለጫዎች*

17 የMCPS የመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች የብሄራዊ ግኝት ስኮላርሺፕ የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪዎች
MCPS የተሻለ ድርጣቢያ ጀመረ፤ አዲስ የሞባይል መተግበርያ
Broad Acres Elementary School በቀድሞ ርእሰመምህር JoAnn Leleck (ጆአን ለሌክ) ክብር እንደገና ተሰየመ